# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የአገልግሎት መሪዎችና የቃል አገልጋዮች ስብሰባ

በሚቀጥለው ሳምንት ከፕሮግራም በኋላ የአግልግሎት መሪዎችና የቃል አገልጋዮች ስብሰባ እንደሚኖር ሽማግሌዎች ያሳስባሉ።

### የአርብ ፕሮግራም

ዘወተር አርብ በሚኖረን የጸሎትና የቃል ፕሮግራም ላይ በመገኘት እንድንካፈል ቤተ ክርስቲያን ታበረታታለች። ጌታ ይባርካችሁ!

### የአገልግሎት ሪፖርት

የአገልግሎት መሪዎች የ2017 የአገልግሎት ሪፖርትና የ2018 እቅዶችን ለሽማግሌዎች በጽሑፍ እንድታቀርቡ በጌታ ፍቅር ሽማግሌዎች ያሳስባሉ።

### አገልግሎት

የድምጽና የምዚቃ መሳሪያዎችን በማስተካከል ለማገልገል የምትፈልጉ ዔሊያስን ወይንም ሽማግሌዎችን እንድታነጋግሩ እንጠይቃለን። በሌሎች አገልግሎቶችም ለማገልገል የምትፈልጉ ሽማግሌዎችን እንድታነጋግሩ እናበራታታለን።

“ወደ ውጭም አውጥቶ:- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው።
እነርሱም:- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።” (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት:-
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0194 (ወ/ም አያሌው)
773-910-0485 (ወ/ም ፒተር)
773-961-5332 (ወ/ም ጌቱ)
773-739-0437 (ወ/ም ሰለሞን)

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| | | |
|---|---|---|
| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |

“እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ” ሉቃስ 2፡10




*“ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው።”*
*(መዝ. 119፡105)*

| Chicago Yemsrach Evangelical Church<br>4455 N. Seeley Avenue<br>Chicago, IL 60625 | መደበኛ ፕሮግራሞች<br>እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.<br>አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m. |
|---|---|
| **February 11, 2018** | **የካቲት 4፣ 2010 ዓ.ም.** |

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................ | ወንድም ሰለሞን ወመን |
| አምልኮ...................... | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ሰለሞን ወመን |
| ቃል ............. | ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### የሳምንቱ ጥቅስ

"የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፥ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል።"

(ዕብ. 4፡12)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመን | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### "ቦነስ" ይጨመራል።

*"እንግዲህ፦ ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ...ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።"*(ማቴ. 6፡33)

አንዳንድ መስሪያ ቤቶች ለሰራተኞቻቸው በአመቱ መጨረሻ ቦነስ ይሰጣሉ። ቦነስ ደመወዝ አይደለም። ነገር ግን በደመወዝ ላይ የሚጨመር ነው። ሰራተኛም ሲሰራ የሚሰራው ለቦነስ ሳይሆን ለደመወዝ ነው። ነገር ግን መስሪያ ቤቱ ትርፋማ ከሆነ የሰራተኞቹን በጎ ጥረት ለማመስገን ቦነስ ሊሰጣቸው ይችላል።

መጽሐፍ ቅዱስ ዋና ነገር እንድፈልግ ይመክረናል። ለክርስቲያን ዋና ነገር የእግዚአብሔርን ጽድቅና መንግስት መፈለግ ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔር ቅድሚያ ያደረገ ሕይወት ማለት ነው። በሕይወታችን ዋና ያደረግነው ነገር እግዚአብሔርን መፈለግ ከሆነ እግዚአብሔር ከሚያስፈልገን ነገር ሁሉ አያጎድለንም። እኛ እግዚአብሔርን ስንፈልግ እግዚአብሔር ደግም አባት ነውና ለልጆቹ በምድር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ያዘጋጃል። ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ ማን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? እያልን እንዳንጨነቅ ያስተምረናል። ለእነዚህ ጉዳዮች የሚጨነቁት የማያምኑ ሰዎች ናቸው። የዚህ አለም ሰዎች ትልቁ የሚኖሩበት አላም ምድራዊ ፍላጎትን ለማሳካት ነው። ሕይወታቸውን የሚመራው የማይሞላ የፍላጎት ቋት ነው። ፍላጎት አይረካም። ሁልጊዜ እልፍ ብሎ የሚገኝ ኢላማ ነው። ስለዚህ የማያምን ሰው የሕይወቱ አላማ ምድራዊ ከሆነው ነገር አያልፍም።

ክርስትና ግን የሚጀምረው ከሙላት ነው። በብሉይ ኪዳን ንጉስ ዳዊት "እግዚአብሄር እረኛዬ ነው የሚያሳጣኝ የለም" በማለት ዘምሯል። (መዝ. 23፡1) መዝሙረኛው የሚለው እግዚአብሔር ካለኝ ሙሉ ነኝ። ፍላጎቴ ረክቷል ነው። ሰው ፍላጎቱ የሚረካው በእግዚአብሔር ላይ ሲያርፍ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ያለው ሰው መሰማሪያ አለው፣ የእረፍት ውሃ አለው፣ ጥበቃ አለው፣ ሰላም አለው፣ በረከት አለው፣ ተስፋ አለው ... ሁሉ አለው። በአዲስ ኪዳንም መጽሐፍ ቅዱሳችን በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከቶች ሁሉ እንደተባረክን ይናገራል። (ኤፌ1፡3) ቃሉ የሚለው እንባረካለን ሳይሆን ተባርከናል ነው። አሁን ተባርከናል። አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን። አሁን በክርስቶስ ደም ቤዛነት አግኝተን ጸድቀናል። አሁን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናል። አሁን አይምሮን ሁሉ የሚያልፍ ሰላም አለን። አሁን በመንፈስ ቅዱስ ታትመናል። አሁን ለትልቅ ተስፋ ተጠብቀናል። አሁን ተባርከናል።

ወገኖቼ፦ እኛ የምንኖረው ሕይወት እግዚአብሔርን ራሱን ማለትም የርሱን ጽድቅና መንግስት የሚፈልግ ነው። ይህ ሲሆን ቦነሱ (የሚበላው፣ የሚጠጣው፣ የሚለበሰው፣ ትዳሩ፣ ስራው... ወዘተ) ይጨመራል። እንደ አብርሃም እግዚአብሔርን ከመረጥን፡ ቀኙም፣ ግራውም ለምለም ነው። ለእርሱ እንጂ ለበነሱ አንኑር። እግዚአብሔር በማስተዋል ይባርከን። አሜን!